

ፎቶግራፍ: KARI NELSON

# የመጨረሻ የግምገማ ሪፖርት

## የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ወተር አሊየንስ ፕሮግራም ግምገማ

የውሃ፣ የአከባቢና የጤና አጠባበቅ (WASH) የድህረ ትግበራ ግምገማዎች አካል—ወተር ኮሚውኒኬሽን ኤንድ ኖውሌጅ ማኔጅመነት (CKM) ፕሮጀክት

ግንቦት 1 ቀን 2010 ዓ.ም

ይህ ሰነድ በሲኬኤም ፕሮጀክት ስር ለዩኤስኤአይዲ በኢኮዲት ኤልኤልሲ እና ሶሻል ኢምፓክት ኢንክ ተዘጋጀ።አይዲኪው ቁጥር ኤኤይዲ-ኦኤኤ-አይ-1400069፣ የስራ ትእዛዝ ቁጥር-ኤአይዲ-ኦኤኤ-ቲኦ-15-00046

## ማጠቃለያ

**ዓላማ እና አጠቃላይ እይታ**

በኢትዮጵያ የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅን ለማሻሻል ለአስርት ዓመታት ጥረቶች ቢደረጉም የዘርፉ አመላካቾች እንደሚያሳዩት አፈፃጸሙ በዓለም ውስጥ ካሉት ዝቅተኞች ተርታ መሆኑን ቀጥሏል። እስከ 2007 ዓ.ም ባለው ጊዜ በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኘው ሕብረተሰብ የዕለት ተዕለት ኑሮን ለማካሄድ በሚያስችል ደረጃ የውሃ አቅርቦት ያገኘው 30 በመቶ ብቻ ሲሆን የተሻሻለ እና የጋራ ያልሆነ መፀዳጃ ተጠቃሚ 4 በመቶ ብቻ ነበር። በተጨማሪም 99 በመቶ የሚሆነው የእጅ መታጠቢያ አቅርቦት አልነበረውም።[1] በኢትዮጵያ[2] በየዓመቱ ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ከ14,000 በላይ ህፃናት በተቅማጥ በሽታ ምክንያት የሚሞቱባት አገር እንደመሆኗ መጠን የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ዕድገት እንቅስቃሴዎች ውጤታማ፣ ብቁ እና ዘላቂ ለውጦችን የሚያመጡ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ልክ ከሰሃራ በታች እንዳሉ ሌሎች ሃገሮች ሁሉ ዘላቂነት አለመኖር ለኢትዮጵያም ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል። ለምሳሌ በ2002/2003 ዓ.ም የተደረገው የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ (WASH) ብሔራዊ ቆጠራ 25 በመቶ የሚሆኑት የውሃ ጣብያዎች ሙሉ በሙሉ ከአገልግሎት ውጪ እንደነበሩ ጠቁሟል።[3] ምንም እንኳ በቂ መረጃ ባይኖርም የውሃ ጣብያዎች ብለሽት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና አንዳዶቹ የውሃ ጣብያዎች ከጥቅም ውጪ የሚሆኑት በተገነቡ በጥቂት ዓመታት ውስጥ መሆኑን መረጃው ያሳያል።[4] ይህም ሁኔታ የገንዘብ እና የጊዜ ብክነት ከማስከተሉም በለይ በማህበረሰቡ ላይ ቅሬታ እና አስጊ የጤና ሁኔታዎች አስከትሏል።

የአሜሪካ የልማት ተራድኦ ደርጅት (ዩኤስኤአይዲ) እነዚህን የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ እንቅፋቶችን ለማስወገድ ዘላቂ መፍትሔዎችን በመለየት በአለምአቀፍ ደረጃ የሚያካሒደው የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ (WASH) እንቅስቃሴዎች ዘላቂ ተፅእኖ እንዲኖራቸው ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው። ዩኤስኤአይዲ ከዚህ በፊት የነበሩ ፕሮጀክቶች ያመጧቸው ለውጦች ምን ያህል ዘላቂ እንደሆኑ እና እነዚህ ውጤቶች እንዲመጡ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን በመረዳት ወደፊት የሚመጡ ፕሮጀክቶችን ለመቅረፅ እና ለመተግበር የሚያስችሉ ልምዶችን በመቅሰም ተግባረዊ ያደርጋል። ይህ ሪፖርት ከዚህ በፊት በዩኤስኤአይዲ የገንዘብ ድጋፍ በተጠናቀቁ የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ (WASH) እቅስቃሴዎች ልምድ ለመውሰድ ሲባል ከተቀረፀው የስድስት ዙር ድህረ ትግበራ ግምገማዎች ውስጥ የሶስተኛውን ግኝት ያቀርባል። ይህ የሚሊኒየም ወተር አሊየንስ ኢትዮጵያ ፕሮግራም (ሚወአ-ኢፕ) ግምገማ ከገጠር የውሃ ጣብያ ግንባታ እና እድሳት፣ ማህበረሰቡ የውሃ ጣብያዎችን ማስተዳደር እንዲሁም ከአሳታፊ የአከባቢ እና ጤና አጠባበቅ ትምህርት ጋር የተያያዙ የረዥም ጊዜ ውጤቶች ለመማር እድል ይከፍታል።

የሚሊኒየም ወተር አሊየንስ ኢትዮጵያ ፕሮግራም ከመጋቢት 1996 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 2002 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ከዩኤስኤአይዲ በተገኘ 4,677,670 ዶላር እና በሚሊኒየም ወተር አሊየንስ  በተደረገ የ2,382,972 ዶላር የወጪ መጋራት በ24 የኢትዮጵያ የገጠር ወረዳዎች በስምንት ድርጅቶች ጥምረት ተግበራዊ ሆኗል። የሚሊኒየም ወተር አሊየንስ ህብረት የውሃ ጣብያዎችን የገነባ እና ያደሰ ሲሆን በማህበረሰብ ደረጃ ያሉ የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎችን የውሃ ጣብያዎችን እንዴት ማስተዳደር እንዳለባቸው አሰልጥኗል። ህብረቱ ከዚህም በተጨማሪ የአሳታፊ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ትራንስፎርሜሽን (Participatory Hygiene and Sanitation Transformation -PHAST) ዘዴን በዋነኝነት በመጠቀም የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ትምህርት የሠጠ ሲሆን የቤተሰብ እና የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች (የተሻሻሉም ያልተሻሻሉም) ግንባታዎችንም ደግፏል።

**የግምገማው ወሰን**

ግምገማው ስድስት ቁልፍ ጥያቄዎችን መልሷል፡

1. **የውሃ ተደራሽነት:** ከተጠናቀቁ ከሰባት ዓመታት በላይ የሆናቸው ሚወአ-ኢፕየውሃ አገልግሎት መስጫዎች የአገልግሎት ደረጃ ምን ያህል ነው?
2. **የውሃ አጠቃቀም:** የማህበረሰቡ አባላት ምን ያህል ከውሃው ተጠቃሚ ናቸው?
3. **የውሃ ጣብያ አስተዳደር:** የውሃ አገልግሎት መስጫዎች ጥገናና እንክብካቤ ከፕሮግራሙ ትግበራ በኋላ እንዴት እንዴት ነበር?
4. **የመፀዳጃ ቤት እና የእጅ መታጠቢያ አጠቃቀም:** በፕሮጀክቱ ድጋፍ የተገነቡ የቤተሰብ እና የጋራ መፀዳጃ ቤቶች እና የእጅ መታጠቢያ ግንባታዎች በአሁኑ ጊዜ በምን አይነት ሁኔታ ይገኛሉ? ምን ያህልስ በአግባቡ ተይዘውና ተጠግነው አገልገሎት እየሰጡ ነው?

---

[1] ደብሊውኤችኦ/ዩኒሴፍ.2017.ፕሮግረስኦን ድሪንኪነግ ዎተር፣ ሳኒቴሽን ኤንድ ሃይጂን፡ 2017 አፕዴት ኤንድ ኤስዲጂ ቤዝላይነስ። መሠረታዊ የውሃ ተደራሽነት ከተሻለ የውሃ ምንጭ የሚገኝ የመጠጥ ውሃ ተብሎ የተገለፀ ሲሆን ይህ የሚሆነውም የሰልፍ ሰዓቱን ጨምሮ ውሃውን ለማምጣት የደርሶ መልስ ሰዓቱ ከ30 ደቂቃ ያልበለጠ ከሆነ ነው።

[2] ደብሊውኤችኦ.2016. ግሎባል ሄልዝ ኦብዘርቫቶሪ። http://apps.who.int/gho/data/view.main.ghe1002015-ETH?lang=en

[3] የኢትዮጵያ መንግስት የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር. ኤፕሪል 2013. *ምኒተሪነግ ዎተር ሰፕላይስ ሴንድ ሳኒቴሽን ኢን ኢትዮጵያ።* በታመነ ሐይሉ ደበላ የቀረበ። https://www.slideshare.net/ircuser/2-hailu-nwi-kpi-msf2

[4] ኢምፕሩቭ ኢንተርናሽናል. 2010. ስታስቲክስ ኦን ዎተር ፖይንት ፌይሊየርስ ዌብ ፔጅ።
http://www.improveinternational.org/2012/10/25/sad-stats/

5. **የህዝብ መፀዳጃ ቤት አስተዳደር:** ህብረተሰቡ የሚሊኒየም ወተር አሊየንስ ኢትዮጵያ ፕሮግራም ድጋፍ የተገነቡትን የህዝብ የአከባቢ ንፅህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጫዎችን ለማስተዳደር እና ውጤቶቹን ለማስቀጠል ምን ዓይነት የአሰራር እና ገንዘብ ማግኛ ዘዴዎችን ተጠቅሟል?
6. **ለምን?** ለእያንዳንዱ ዓይነት የውሃ እና የአከባቢ ንፅህና አገልግሎት በዘላቂነት መቆየት አስተዋፅኦ ያደረጉ ወይም ያዳከሙ ነገሮች ምንድን ናቸው?

### ንድፍ

ግምገማው የተለያዩ ዓይነት/ቅይጥ የአጠናን ዘዴ ንድፎችን የተጠቀመ ሲሆን እነዚህም: 64 የግል እና የቡድን ቃለመጠይቆችን፣ 13 የውሃ ጣብያዎችን እና 15 መፀዳጃ ቤቶች ግንባታ ጉብኝት፣ የ10 የውሃ ጣብያዎች የውሃ ጥራት ምርመራ እና ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ቅኝት ናቸው። ይህ ቅኝት በአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር ዞን ያለ የውሃ ጣብያ ቆጠራ መረጃን እና በወረዳ ጤና እና ውሃ ቢሮዎች የሚገኝን የመፀዳጃ ቤት እና የውሃ ጣብያዎችን መረጃ ያካተተ ነው። የግምገማ ቡድኑ ከጥቅምት እስከ ህዳር 2010 ዓ.ም ባሉት አራት ሳምንታት ውስጥ እንቅስቃሴው ከተደረገባቸው 24 ወረዳዎች ውስጥ በሰባቱ መረጃ ሰብስቧል። ሰባቱ ወረዳዎች ከአማራ ክልል እና ከደቡብ ብሄሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ሆን ተብለው የተመረጡ ናቸው። የግምገማ ቡድኑ ከዚህም በተጨማሪ ለተግባሪ አጋር አካላቶች ቃለመጠይቅ ያደረገ ሲሆን አዲስ አበባም ከዩኤስኤአይዲ ሰዎች ጋር ስብሰባዎች አካሂዷል። የግምገማ ቡድኑ የመስክ ስራዎቹን ከመጀመሩ በፊት ሚወአ-ኢፕ እንቅስቃሴ የፅሁፍ መረጃዎችን እና አግባብነት ያላቸውን የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ፅሁፎችን መርምሯል።

## ቁልፍ ግኝቶች

### የውሃ ጣብያዎች: አሁን የሚገኙበት ደረጃ እና ጥቅም

የግምገማ ቡድኑ የውሃ ጣብያዎቹ በአገልግሎት ላይ ስለመሆናቸው፣፣ የውሃ መጠን እና አጠቃቀም፣ የውሃ ጥራት፣ ተደራሽነት እና አስተማማኝነትን ጨምሮ ሌሎች ሁኔታዎችንም ገምግሟል።[5]

***ከተጎበኙት የውሃ ጣብያዎች በርካታዎቹ መሠረታዊ አገልገሎት የመስጠት ችግር ያለባቸው ናቸው፥*** በቃለመጠይቅ እና ቀጥታ በተደረጉ ጉብኝቶች ወቅት የውሃ ጣብያዎቹ የአገልግሎት ችግሮች ችግሮቹ ታይተዋል። የግምገማ ቡድኑ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት ከተጎበኙት 13 የውሃ ጣብያዎች የሚሰሩት አምስቱ ብቻ ነበሩ። ሶስቱ ሙሉ ለሙሉ አይሰሩም። በአማራ ክልል የሚገኙ 4,352 የውሃ ጣብያዎችን የሚወክል ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ጥንቅር እንደሚያሳየው ከእነዚህ ሚወአ-ኢፕየተሰሩ የውሃ ጣብያዎች ውስጥ ከ2008 ዓ.ም ላይ እየሠሩ የነበሩት 44 ከመቶ ብቻ ናቸው። በተመሳሳይ ጊዜ በሌላ ተግባሪዎች/ድርጅቶች የተሰሩ የውሃ ጣብያዎች 53 በመቶ የሚሰሩ ሲሆን ይህም በሚወአ-ኢፕየተሰሩ የውሃ ጣብያዎች በዚያው የገጠር አከባቢ ካሉ ሌሎች የውሃ መሠረተ ልማቶች አንፀር ሲታዩ በዝቅተኛ ደረጃ እየሰሩ ሊሆን እንደሚችል ያመላክታል።

***የውሃ ጣብያዎቹ በአግባቡ ጥቅም ላይ የዋሉ እና አብዛኞቹ በርከት ያለ የውሃ መጠን እያቀረቡ ቢሆንም ብዙ ሰዎች ሌሎች የውሃ አቅርቦቶችን ይጠቀማሉ፥ ይጠቀማሉ።*** የማህበረሰቡ አባላት በሚወአ-ኢፕ የተገነቡ የውሃ ጣብያዎች አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ የማህበረሰቡ አባላት በተለይ ለመጠጥ ውሃ በየቀኑ ይጠቀምበቸዋል። ከተጎበኙት ዘጠኝ የውሃ ጣብያዎች ውስጥ ስድስቱ የውሃ ፍሰት ልኬታቸው በንድፈሐሳብ ደረጃ ለማህበረሰቡ ለቤት ውስጥ ጥቅም የሚውል በቂ የሆነ ውሃ ያቀርባሉ ተብሎ ይታሰባል። ይህ ሆኖ እያለ ግን ብዙ ቤተሰቦች የውሃ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ከሚወአ-ኢፕ የውሃ ጣብያዎች በተጨማሪ ሌሎች የውሃ አቅርቦቶችን በ ይጠቀማሉ። ሰዎች ለምን በርካታ የውሃ አቅርቦቶች እንደሚጠቀሙ እንዲሁም ኤምደብሊውኤ-ኢፒ ውህን ለበርካታ አገልግሎት ሰለማዋል የነበረው እቅድ እንዴትእንደነበር ብዙም አይታወቅም።

***አብዛኛዎቹ የውሃ ጣብያዎች የውሃ ጥራት ደረጃን ኢያሟሉም፥*** ሰዎች የኤምደብሊውኤ-ኢፒ የውሃ ጣብያዎችን እንደ ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ምንጭ አድርገው ቢያምኑም አብዛኞቹ የውሃ ጣብያዎች በየጊዜው የውህ ጥራት ምርመራ እየተደረገላ ቸው አልነበረም። በዚህ ጥናት በተደረገው የውህ ጥራት ምርመራ አብላጫዎቹ (ከአስሩ ሰባት የሚሆኑት) በኢኮላይ ባክቴሪያ የተበከሉና ጥራት ያለው ውሃ የማያቀርቡ ሆነው ተገኝተዋል።

***በአብዛኞቹ የውሃ ጣብያዎች ወረፋ ተደራሽነቱን ኢዴጋ ውስጥ ከቶታል፥*** መላሾች ዉሃ ለማግኘት ከ30 ደቂቃ በላይ መጠበቅ እናዳለባቸው በተደጋጋሚ ገልፀዋል፣ በውሃ ጣብያዎቹ የተደረገው ጉብኝትም በአማካኝ 10 የውሃ እቃዎች ወረፋ በየጣብያውእንዳለ ያረጋገጠ ሲሆን አንድ የመቅጃ ጊዜም በአማካኝ 2.5 ደቂቃ በውሃ እቃበመሆኑ የመጠበቂያ ጊዜውን ወደ መደበኛው ዉሃ ቀድቶ

[5] ፍቺዎች: መሠረታዊ የውሃ ጣብያ መስራት የሚለካው ውሃ ጣብያዎቹ በጉብኝት ወቅት ውሃ ያቀረቡ ከሆነ ነው። የውሃ ብሃት ሲባል ለአንድ ሰው በቀን 20 ሊትር ውሃ የሚለውን የዩኤስኤአይዲ መስፈርት ለማለት ነው። የውሃ ጥራት ማለት ከብክለት (ምሳሌ-ኢኮላይ) እና ከኬሚካል (ምሳሌ-ፈሎራይድ እና አርሰኒክ) ነፃ የሆነ የውሃ አቅርቦት ማለት ነው።የውሃ ጣብያ ተደራሽነት ሲባል ውሃ ቀድቶ ለመመለስ ከ30 ደቂቃ መብለጥ የለበትም ሲል ዩኤስኤአይዲ የሰጠውን ፍቺ ማት ነው። የውሃ አስተማማኝነት ሲባል አንድ የውሃ ጣብያ አመቱን ሙሉ ያለ ራሽን እና ወቅታዊ ጉድለት ውሃ ማቅረብ የሚላውን የዩኤስኤአይዲ HL.8.1-3 የተባለውን ጠቋሚ ማለት ነው። የውሃ ጣብያ ጥቅም ሲባል የውሃ ጣብያውን ማን ይጠቀመዋል፣ እስከምን ደረጃ እና ማን አይጠቀመውም የሚለውን ለመግለፅ ነው

ላማምጣት ወደ ሚፈጀው የ30 ደቂቃ አከባቢ ያደርገዋል። ከተጎበኙት ቦታዎች በአብዛኞቹ የመጓጓዣ ጊዜን ተጨምሮ በ30 ደቂቃ ውስጥ ውሃ ቀድቶ መጨረስ አይቻልም።

***የዉሃ አስተማማኝነት ችግር ቢታይም ችግሩ ከወቅት ጋር የተያያዘ የውሃ መጠን መዋዥቅ ችግር ሳይሆን ከጥገና ጋር የተያያዘ ነው።*** የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎች በተለምዶ ሁለት ሳምንታት ያህል የሚፈጁ ብዙ ጥቃቅን ጥገናዎችን ያካሄዱ ቢሆንም ጉብኝቱ በተደረገበት ወቅት የመስራት አቅምን የሚገድቡ ጥገናዎች ከገንዘብ ድጋፍ እጥረት ጋር በተያያዘ ምክንያት አልተጠናቀቁም ነበር። በወቅት ምክንያት የሚከሰት የውሃ መጠን መዋዠቅ የታየው ከተጎበኙት ቦታዎች በጥቂቱ ብቻ ነው።

## የአከባቢ ፅዳት እና እጅ መታጠብ: አሁን ያለበት ሁኔታ እና አጠቃቀም

***አብዛኛው ቤተሰብ እንዳስፈላጊነቱ መፀዳጃ ቤቶችን የቀየረ ቢሆንም በአጠቃቀም ላይ ግን ወጥነት የሚጎል ሲሆን ተጠቃሚዎችም በአከባቢ ፅዳት ዙሪያ መሻሻል አላመጡም፥*** *ከተደረጉት ቃለመጠይቆች እና በጉብኝት ወቅት በቀጥታ እንደታየው* በሚወአ-ኢፕ አማካኝነት የአከባቢ ጥበቃ ድጋፍ ያገኙት አሁንም ቢሆን መፀዳጃ ቤታቸው በሞላ ጊዜ ይቀይራሉ። ሆኖም ግን አብዛኞቹ ቀድሞ የተሰሩት እስካሁን ጥቅም ላይ ያሉ ሲሁን ቅያሪዎቻቸው ግን በአግባቡ ባለመያዛቸው የተከፋፈቱ እንዲሁም ለአደጋ አጋላጭ በመሆናቸው ሰዎች እንዲጠቀሟቸው አያበረታቱም። አብዛኛዎቹ የተጎበኙት መፀዳጃ ቤቶች ያልተሸሻለ ንድፍ ያላቸው ሲሆን ተጠቃሚዎቹም መጸዳጃ ቤት ከመቀየር በቀር ተገቢውን የንጽህና አጠባበቅ ደረጃ ተከትለው የሚጠበቀውን የመፀዳጃ ቤቶች ማሻሻያ በማድረግ ረገድ እድገት አላሳዩም።

ምንም እንኳ የመፀዳጃ ቤቶች ባለቤቶች መፀዳጃ ቤቶቹን እየተጠቀሙ እንደሆነ በሰፊው ቢገልፁም አጠቃቀሙ እንደተገለፀው ከፍተኛ እንዳልሆነ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች ጠቁመዋል፤ የተደረገው ጉብኝትም ይህንኑ ይደግፋል። የመፀዳጃ ቤት ጠቀሜታ ትምህርት ቢሠጥም ከመፀዳጃ ቤት ግንባታ አንፃር ጥቅም ላይ የሚውልበት መጠን ወደኋላ የቀረ ነው። የመፀዳጃ ቤቶች ሽፋን መጠን እንደቀጠለ መሆኑን የሚያሳዩ ጠቋሚዎች ቢኖሩም በአጠቃቀም ዙርያ ያሉ ልምዶችን ለመቀየር ግን ከፍተኛ ስራ መሠራት ይኖርበታል።

***ሁሉም የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች እያሰሩ አይደለም፥*** በአሁኑ ወቅት በሚወአ-ኢፕ ድጋፍ የተደረገላቸው የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች እንዳቸውም አገልግሎት እየሰጡ አይደለም። ሰዎች እንጨቶቹን እየገነጠሉ ለማገዶነት ያዋሏቸው ሲሆን ይህም የማህበረሰቡ ጊዜያዊ የማገዶ ፍላጎት ታስቦ ከነበረው የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች ፍላጎት በላይ መሆኑን ያሳያል።

***ሰዎች እጅ የሚታጠቡበትን መጠን ኢጋናው ሊናገሩ ይችላሉ፥***አብዛኞቹ የመፀዳጃ ቤት ባለቤቶች በየጊዜው እጃቸውን እደሚታጠቡ ቢገልፁም በጉብኝት ጊዜ የተገኘ መረጃ እና ከጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች ጋር የተደረገው ቃለመጠይቅ ይህ የተጋነነ እንደሆነ ያመላክታል። በጉብኝት ወቅት ምንም ዓይነት የእጅ መታጠቢያ ጣብያዎች ወይም ሌሎች ምልክቶች ያልታዩ ሲሆን ሰዎች በየጊዜው እጃቸውን እንዲታጠቡ ለማሳመን ከፍተኛ ችግር እንደሚገጥማቸው የጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች ገልፀዋል።

## ውይይት: ለዘላቂነት እንቅፋት የሆኑ ምክንያቶች

ከላይ የተገለፁት ውጤቶች ላይ ተፅእኖ የሚያደርሱ ብዙ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥም አስተዳደራዊ፣ የገንዘብ፣ ተቋማዊ፣ አከባቢያዊ፣ የመሬት ባለቤትነት እና ማህበራዊ ባህርይ ይገኙበታል።

***አስተዳደራዊ ምክንያቶች፥*** የውሃ ጣብያዎች ዘላቂ አገልግሎት እንዲሰጡ ሚወአ-ኢፕየኢትዮጵያ መንግስት የገጠር ውሃ አቅርቦት ዘዴን በመከተል በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የሰራ ሲሆን የማህበረሰብ አስተዳደር መዋቅሮችን (የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎች) ዘርግቷል። እነዚህ ሁሉ ጥረቶች ተደርገው እና ስልጠናዎች ተሰጥተው የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎች የውሃ ጣብያዎቻቸውን በአግባቡ ለማስተዳደር ተቸግረዋል። የውሃ ጣቢዎች እድሳት እና ጥገና ከፍተኛ ተግዳሮቶች ናቸው። የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎቹ የእድሳትና እና የጥገና ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስችል ግንዘብ ለማግኘት ተቸግረዋል። ይህ ግኝት መሠረተ ልማትን በህብረተሰብ እንዲተዳደር ማድረግ ዘላቂነቱ አስቸጋሪ ነው ከሚሉ ከዚህ ቀደም ከተደረጉ ጥናቶች ጋር ይመሳሰላል።[6] በአማራ ክልል የተደረገ የውሃ ጣብያዎች ቆጠራ እንደሚያሳየው በሚወአ-ኢፕ የሚደገፉ በዛ ያሉ የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎች የአስተዳደር ስልጠና የወሰዱ ቢሆንም ከአቻዎቻቸው ጋር ሲወዳደሩ አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ ነው። ስለ ሚወአ-ኢፕ የስልጠና ጥረቶች መረጃ ባይኖርም የግምገማው ውጤቶች የሚያሳዩት ስልጠናዎቹ ዘላቂነትን ለማረጋገጥ በቂ እናዳልነበሩ ነው።

የህዝብ መፀዳጃ ቤቶችን በተመለከተ ለመጸዳጃ ቤቶቹን ለማደስ ስለታሰበው የአስተዳደር ወይም የገንዘብ መዋቅር ምንም ዓይነት መረጃ የለም።  በግምገማው ወቅት አንድም የህዝብ መፀዳጃ ቤት አለመገኘቱ ግን ታስቦ የነበረው የአስተዳደር ዘዴ ውጤታማ አልነበረ ያሳያል።

***የገንዘብ ሁኔታዎች፥*** የውሃ፣ አከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎቹ የውሃ ጣብያዎቹን እድሜ ለማራዘም የሚረዳ ገንዘብ ማግኘት አለመቻላቸው የውሃ ጣብያዎቹን ውጤታማነት እና ዘላቂነት ጎድቶታል። በክልል እና በወረዳ ደረጃ በግልፅ የሚታይ የክፍያ አሰባሰብ ልዩነት አለ። በአማራ ክልል የሚገኙ የውሃ፣ አከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎች ከደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ጋር ሲነፃፀሩ ጉልህ የሆነ የክፍያ አሰባሰብ ድክመት ታይቶባቸዋል። ለእነዚህ ችግሮች እና በየክልሎቹ ለሚታዩት ልዩነቶች እንደምክንያትነት

[6] ፒተርሰን ኤ ኤንድ ኤም ክሬመር. 2007. “ዋት ዎርክስ ኢን ፋይቲንግ ዲሃሪያል ዲዚዝስ ኢን ዴቨሎፒንግ ካንትሪስ? ኤ ክሪቲካል ሪቪው” ዘ በተርዎርዝ 2016። ግሎባል ስተዲ ኦን ሰስቴይነብል ሩራል ዎተር ሰርቪስ ዴሊቨሪ ሞዴልስ፡ ካንትሪ ብሪፍ ኢትዮጵያ። ወርልድ ባንክ ሪፖርት።

ሊጠቀሱ ከሚችሉት ውስጥ የውሃ፣ አከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎች ደካማ አስተዳደር፣ የተጠቃሚዎች ክፍያ ለመክፈል አለመፈለግ፣ የተጠቃሚዎች መክፈል አለመቻል፣ ቀድሞ የነበረ ለውሃ ያለመክፈል ልምድ እና በአከባቢው የሚገኝ እንደ የወንዝ እና የከርሰምድር ያለ አማራጭ የውሃ ምንጭ መኖር ይገኙበታል።

በቤተሰብ ደረጃ የሚገኙ መፀዳጃ ቤቶች ግንባታ ወይም ማሻሻያ ላይ የሚታየው የተገደበ ዕድገት ከገንዘብ እጥረት እና ከሌሎች ገንዘብ ከሚያስፈልጋቸው ፍላጎቶች ጋር ሲነፀፀር ለአከባቢ ንፅህና ቅድሚያ ካለመሰጠቱ ጋር ይገናኛል። ጥናቶች እደሚሳዩት የገንዘብ እጥረት የእጅ መታጠብ ልምዶች ላይም በተለይም የውሃ እጥረት ባለባቸው አከባቢዎች ላይ ተፅዕኖ አለው። የተደረጉ ቃለመጠይቆች እንደሚያሳዩት በኢኮኖሚያዊ ችግሮች ይሁን ውሀ ጨርሶ በለመመኖሩ ምክንያት የውሃ እጥረት ካለ ሰዎች ውሃን ለእጅ መታጠብያነት ከማዋል ይልቅ ለሌሎች አግልግሎቶች ማዋልን ያስቀደድማሉ።

***ተቋማዊ ሁኔታዎች፥*** ሚወአ-ኢፒ የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎች በየደረጃው ካሉ የመንግስት ቢሮዎች ጋር ተቋማዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ በቂ ጊዜም ሆነ ትኩረት ባለመስጠቱ በአፈፃፀማቸው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል። ለምሳሌ ያህል የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎች ከፕሮጀክት መጠናቀቅ በኋላ የሚሰጥ ስልጠና አለመኖሩን እና የሚደረገውም የውሃ ጥራት ምርመራ ውስን እንደሆነ ገልፀዋል። ዋነኛው ችግር የመንግስት አካላት የውሃ ጣብያዎቹን በመደገፍ ዙሪያ ያላቸው ሚና እና ሃላፊነት ግልፅ አለመሆን ነው። ለምሳሌ ከቃለመጠይቆቹ እንደምንረዳው ከአንድ ተቋም የመጡ ግለሰቦች እንኳን እንደውሃ ጣቢያዎች ጥገና እና የጥራት ምርመራ ያሉ ቁልፍ የድጋፍ እንቅስቃሴዎች የማን ሃላፊነት እንደሆኑ ሲጠየቁ በጣም የተለያዩ ምላሾችን ያቀርባሉ። ይህ የሚና እና የሃላፊነት ግልፅ አለመሆን ከድጋፍ አለመኖር ጋር ተደምሮ በውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎች ደረጃ ያሉትን የአስተዳደር እና የገንዘብ ተግዳሮቶችዘላቂነትን በሚያደናቅፍ መልኩ የተባባሱ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

ከገጠር ውሃ አቅርቦት በተቃራኒ በአከባቢ እና በጤና አጠባበቅ ላይ በተለያዩ የመንግስት ደረጃዎች ያሉ ተቋማዊ ሚናዎች እና ሃላፊነቶች በሚገባ የተደራጁ ሲሆን ሁሉም የቃለመጠይቅ መላሾች የአከባቢ እና ጤና አጠባበቅ ስራዎች በጤና ጽህፈት ቤቶች እና በጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች እንደሚሰሩ ገልፀዋል። የጤና ጽ/ቤቶችና እና የጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች ሚናቸው ግልፅ ቢሆንም ስልጠና እና ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶችን ለመስጠት ዞናቸውን ለማዳረስ የሚያስችል የሰው ሃይል እጥረት መኖር፣ ሩቅ አከባቢዎችን መድረስ አለመቻል እና ሌሎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተመሳሳይ አገልግሎቶች የመኖር ተግዳሮቶች ያጋጥሚቸዋል። ለምሳሌ መንግስት ከሚሰራቸው በርካታ የጤና ስራዎች ውስጥ ከአከባቢ ንፅህና፣ የእጅ ንፅህና እና ከውሃ ደህንነት በላይ ለሌሎች የጤና ጉዳዮች ቅድሚያ ይሰጣል።

***አከባቢያዊ ሁኔታዎች፥ ምንም እንኳ*** አከባቢያዊ ሁኔታዎች ከፕሮጀክቱ (ወይም ከመንግስት) ቁጥጥር ውጪ ቢሆኑም በፕሮጀክት ንድፍ ጊዜ በቅድሚያ እቅድ ሊደረግባቸው እና ቀደም ተብለው ሊታለሙ ይችላሉ። የቃለመጠይቁ መላሾች ለውሃ ጣብያዎቹ የረዥም ጊዜ ስኬት አግባብ የሆኑ ሁለት ቁልፍ አከባቢያዊ ሁኔታዎችን የጠቆሙ ሲሆን እነዚህም ከአየር ንብረት ችግሮች እና ከከርሰ ምድር ውሃ መኖር ጋር የተያያዙ ናቸው። የግምገማው ውጤት እንደሚያሳየው ተግባሪ አጋር አካላቶቹ እነዚህን ችግሮች የውሃ መኖርን በመመርመር እና የውሃ ጣቢያዎች ንድፎች በእነዚህ ውጤቶች መሰረት በማስተካከል በሚገባ ቀርፈዋቸዋል። ይህም በጣብያዎቹ በሚታየው ወቅታዊ የውሃ መጠን አለመዋዠቅ እና በጉድጓዶች አለመድረቅ ይንፀባረቃል።

አከባቢያዊ ሁኔታዎች በክፍያ አሰባሰብ እና በአከባቢ እና ጤና አጠባበቅ ላይም ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ውሃ በብዛት እና በነፃ በሚገኝባቸው አከባቢዎች ክፍያ አሰባሰብ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። የውሃ እጥረት ባለባቸው አከባቢዎች ሰዎች ውሃን ከአከባቢ እና ጤና አጠባበቅ ይልቅ ለሌሎች ጥቅሞች ያውሉታል።

***የመሬት ባለቤትነት ሁኔታዎች፥።*** የመሬት ባለቤትነት ሁኔታዎች በትግበራ ወቅት ጉልህ ትኩረት ያልተሰጣቸው ሲሆን ከትግበራ በኋላ ላለው ዘላቂነት ላይ ግን ችግር ፈጥረዋል። በሚወአ-ኢፒ ተግበራ የመሬት ባለቤትነት ችግሮች በሶስት ጉዳዮች ላይ ተነስቷል 1) የማህበረሰብ የውሃ ጣብያዎች በተሰሩባቸው አከባቢዎች ከቦታ መረጣ እና ለመሬት ባለቤቶች ከሚገባ ካሳ ጋር ተያይዘው ከማህበረሰቡ ጋር የተገቡ ግጭቶች፣ 2) የተከራዮች እና የመሬት አከራዮች በውሃ እና የጤና አጠባበቅ መሠረተ ልማቶች ላይ ለመስራት ማበረታቻ ማጣት እና 3) የመሬት ባለቤቶች በመሬታቸው ላይ የሚገኝን ውሃ የመጠቀም መብት ናቸው*።*

***ማህበራዊ/ባህሪያዊ ሁኔታዎች፥።*** በ2000ዓ.ም የተደረገው የሚወአ-ኢፒ የመጨረሻ ግምገማ እንደሚያሳየው በተግባሪ አጋር አካላቶች መካከል ጥቅም ላይ የዋሉት የባህሪ ለውጥ ማምጫ ዘዴዎች በጣም የተለያዩ ሲሆኑ ዘዴዎቹም በሚገባ ያልተቀመጡ እና የቅንጅት ጉድለትም ይታይባቸዋል። የቃለመጠይቅ መላሾች በአከባቢ እና በጤና አጠባበቅ ያሉ የባህሪ ለውጦች ለማሻሻል ከትግበራ በኋላ ክትትል እና ድጋፍ ማደረግና በቋሚ መልኩ መልእክቶችን ማስተላለፍ ተቀባይነትን ለማሻሻል ይረዳል የሚሉ ሃሳቦችን ያቀረቡ ሲሆን እነዚህ ሃሳቦች በዙሪያው በተፃፉ ፅሁፎች ይደገፋሉ።[7] ለዘላቂነት ሲባል ይህ ሚና በማህበረሰቡ ወይም በመንግስት ኣካላት መወሰድ አለበት።

---

[7] ዋንት ላንድ. ዲ. ቢ ኤንድ ቲ. ፓልሜሮ. 2009. (ኢዲ). ሪተርባነድ ኤል. "ፒሪየዲክ ፕሮምፕትስ ኤንድ ሪማይንደርስ ኢን ሄልዝ ፕሮሞሽን ኤንድ ሄልዝ ቢሄቪየር ኢንትርቬንሽንስ፡ ሲስተማቲክ ሪቪው". ጆርናል ኦፍ ሜዲካል ኢንተርኔት ሪሰርች፣ 11(2) ኤንድ ኦሪ ኤም ኤም፣ ስሚዝ ኤን ሚየር ኤንድ ኤም ሬንክል.2010. " ዘ ሳይንስ ኦፍ ሰስቴይኒንግ ሄልዝ ቢሄቪየር ቼንጅ፡ ዘ ሄልዝ ሜንቴይነንስ ኮንሶርቲየም" አሜሪካን ጆርናል ኦፍ ሄልዝ ቢሄቪየር፣34(6), 647-659።

**ቁልፍ አንደምታዎች እና ጥቆማዎች**

1. **የመንግስት አካላት ዘላቂነት ያለው የዕድሳትና እና የክትትል ሥራ ላይ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ።** ጠንካራ ተቋማዊ ድጋፍ ለማረጋገጥ መንግስት የውሃ ጣብያዎች/የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎችን በመደገፍ ረገድ ሊኖረው የሚገባውን ሚና እና ሃላፊነት ግልፅ ለማድረግ እንዲሁም የመንግስት ቢሮዎች ድጋፍ ለመስጠት ያጋጠማቸውን የገንዘብ እና የሎጂስቲክ ችግሮችን ለማቃልል የአሜሪካ የልማት ተራድኦ ድርጅት ለመንግሰት ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል።
2. **የማህበረሰብ አስተዳደር ሞዴልን የተሸሻለ ለማድረግ አማራጭ የገጠር ውሃ ዘዴዎችን ማጥናት።** በዘርፉ የተፃፉ ፅሁፎች እና የዚህ ግምገማ ውጤት እንደሚያሳየው በገጠር የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ መሠረተ ልማቶች ዙርያ ከፍተኛ የዘላቂነት ችግር ያለ ሲሆን ይህም በጥቅም ላይ የዋለው ዘዴ የመጨረሻው ውጤታማ ዘዴ ላይሆን እንደሚችል ያሳያል።ስለዚህ የአሜሪካ የልማት ተራድኦ ድርጅት) በማህበረሰብ የሚተዳደሩ የገጠር የውሃ መሰረተ ልማት እንቅስቃሴዎችን ከመተግበሩ በፊት የሞዴሎቹን ውጤታማነት እና ዘላቂነት መመርመር ይኖርበታል።
3. **የውሃ መሠረተ ልማትን እና ታሪፍ ከመተመን በፊት የአገልግሎት ዘመን ወጪዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት።** በስራው እንቀስቃሴ፣ በዕድሳት እና ጥገና ላይ የሚሳተፉ አካላት በሙሉ ሚናቸውን ሊያሳኩበት የሚያስችላቸው በቂ ግባአት ያስፈልጋቸዋል። ከላይ በተራ ቁጥር 1 እንደተጠቆመው የመንግስት ተቋማት የአገልግሎት ዘመን ወጪዎችን የመደገፍ ሚናቸውን እንዲወጡ ከማስቻል በተጨማሪ የውሃ፣ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ኮሚቴዎች የውሃ ጣብያ የዕድሳት፣ ጥገና እና ቅየራ ሙሉ ወጪን መሠረት በማድረግ በጀት እንዲያዘጋጁ ማድረግ እና ታሪፍ መወሰን እንዲችሉ ሊሰለጥኑ ይገባል።
4. **አዲስ የውሃ አቅርቦት ፕሮጀክቶች በሚነደፉበት ወቅት የውሃ ተጠቃሚዎችን የውሃ ፍላጎት እና የውሃ ምንጩን ዳሰሳ ማድረግ።** የሁሉንም የማህበረሰብ አካላት የውሃ ፍላጎት በመረዳት እቅድ ማውጣት በአዲስ የውሃ አቅርቦት እንቅስቃሴዎች ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተጠቃሚዎች ውሃ እንዲያገኙ በሚያስችል መልኩ ለመንደፍ ይረዳል።
5. **ደካማ የሆነ የአከባቢ እና የግል ንፅህና ልማዶች ባሉባቸው አከባቢዎች ቀለል ባለ ትምህርት ላይ የተመሰረተ የባህሪ ለውጥ ሞዴል ፋንታ ጠንካራ እና ወጥ የሆነ አማራጭ ዘዴዎችን መፈለግ።** የመፀዳጃ ቤት ያለመኖር እና እጅ አለመታጠብ የሚያመላክተው ሚወአ-ኢፐ ተግበራዊ ያደረገው አሳታፊ የአከባቢ እና የጤና አጠባበቅ ትራንስፎርሜሽንን (PHAST) መሰረት ያደረገ ዘዴ ትክክለኛ የሆነ የባህሪ ለውጥ ለማምጣት በቂ አልነበረ ነው፡፡ ምናልባት ሌሎች ዘዴዎች ወይም አሰራሮች የበለጠ ውጤታማ ሊሆኑ ስለሚችሉ መመርመር ወይም መፈተሽ ይኖርባቸዋል።
6. **ሰዎች ለውሃ ጥራት ያለቸውን ግንዛቤ እና ግምት ማሳደግ፡፡** የአሜሪካ የልማት ተራድኦ ድርጅት እና ተግባሪ አጋር አካላቶች ወደፊት በሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ለማህበረሰቡን የውሃ ጥራት ትምህርት በሚስጡበት ጊዜ ትምህርቶቹ የውሃ ጥራት (ከሚታዩ እና ከማይታዩ የውሃ በካዮች) አስፈላጊነትን እና የብክለት ምንጮችን የመሳሰሉ ነጥቦችን ያካተቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ትምህርቶቹ ማህበረሰቡ በውሃ ምንጮች እና በውሃ ጣቢያዎች ላይ ብክለትን ለመለካት እና ለመከላከል ብሎም ለማጥፋት በሚያስችሏችው ዘዴዎች ወይም ስትራቴጂዎች ላይ ብቁ እንዲሆን ማድረግ አለባቸው፡፡
7. **የውሃ አቅርቦት የስራ እንቅስቃሴ በሚነደፍበት እና በሚተገበርበት ወቅት ሁሉ የመሬት ይዞታን ጉዳይ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡** በአግባቡ የተጠኑ ዘዴዎችን በመከተል የመሬት ይዞታን ጉዳይ ለምሳሌ የውሃ ጣብያን ለመገንባት መረጣ ፣ ካሳ እና ሊነሱ የሚችሉ ግጭቶችን ስለመፍታት በማያሻማ እና ግልፅ በሆነ መንገድ በደንብ የተዘጋጀ የተግባር እቅድ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህም ሁልጊዜ የሚተገበር ደረጃውን የጠበቀ አሰራር መሆን አለበት።